# የትምህርትና ስልጠናው ዘርፍ አዳዲስ እመርታዎች

በክሪ ኡመር

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት በአስከፊ ድህነትና ኋላ ቀርነት ውስጥ ኖሯል። ይህ ደግሞ የውጭ ኋይሎችን እርዳታና ድጋፍ እየጠበቀ ከመኖር የተሻለ አማራጭ እንዳይኖረው ያስገደደው እንደነበር ለማንም ግልፅ ነው።

ሆኖም ባለፉት ጊዜያት ህዝቡ ከውጭው አለም እንዲቸረው ይጠብቅ የነበረው የእህል አሊያም የገንዘብ ድጋፍና ዕርዳታን ብቻ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም በሀገራችን በተለያዩ ደረጃዎች በሚካሄዱ የልማት ስራዎች ውስጥ የእውቀት ድጋፎችን የሚሻም ነበር።

የዚህ ችግር ዋነኛው መንስኤ ደግሞ በሃገራችን ልማታዊ አስተሳሰብ ያለው፣ በእውቀትና ክህሎት የታነፀ በቂ የሰው ሃይል ሊፈራ አለመቻሉ እንደሆነ አያከራክርም። እስቲ በልማቱ መስክ ላይ ተሰማርቶ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት የሚችል የሰለጠነ የሰው ሃይል በጥራትና በበቂ ሁኔታ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ባለፉት ጊዜያት በህብረተሰባችን ውስጥ ይንፀባረቅ ስለነበረው አንድ እውነታን በማሳያነት ላንሳ።...

...ባለፉት ጊዜያት በሀገራችን በተለያዩ ደረጃዎች ይካሄዱ የነበሩ የልማት ስራዎችን ጎብኝተን አልያም በመገናኛ ብዙሃን ተከታትለናቸው ይሆናል። ከእነዚህም መካከል በግዙፍነታቸው አሊያም በዘመናዊነታቸው እንግዳ የሚሆኑብን አይታጡም።

እዚህ ላይ ለማንሳት የምፈልገው ጥያቄ ታዲያ 'እነዚህ ስራዎች የኢትዮጵያውያን እውቀት አርፎባቸው ለውጤት የበቁ ናቸው' ብለን የምንገምት ስንቶቻችን ነበርን? የሚለውን ነው። ...እርግጠኛ ነኝ በርካቶቻችን እንደእነዚህ አይነቶቹን ስራዎች ስንመለከት ቀድመን የምናስበው የውጭ ሙያተኞች እውቀት የፈሰሰባቸው እንደሆኑ ስንገምት ኖረናል።

በነገራችን ላይ ይህ አይነቱ አመለካከት መኖሩ ተገቢ አልነበረም የሚል ግምት የለኝም። ምክንያቱም ለረጅም ጊዜያት በልማቱ መስክ ላይ ውጤት ማምጣት የሚችል በእውቀትና በክህሎት የዳበረ በቂ የሰው ሃይል ሳይገነባ ቆይቷል።

በልማቱ ስራ ላይ በወሳኝ ጉዳዮች ዙሪያ  የውጭ ሙያተኞች እውቀት ጥገኛ ለመሆን የተገደድነውም በዚሁ ሳቢያ እንጂ ሃገሪቱ ከአለም ገበያ እውቀት ለመግዛት የምታፈሰው ዶላር ስለተረፋት አልነበረም።

ይሁን እንጂ ይህ ለረጅም ጊዜያት ከእህልና ገንዘብ ባልተናነሰ መልኩ የእውቀት ጥገኛ ሆነን የተጓዝንበት ምዕራፍ መፍትሄ ሳይበጅለት አልቀጠለም። ክብርና ሞገስ ለታላቁ መሪያችን ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ይሁንና ይህ ሁኔታ በአጭር ጊዜያት ውስጥ ከመሰረቱ የሚለወጥበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።

ሁላችንም እንደምናውቀው ባለራዕዩ መሪያችን የዚህች ሃገር ዋነኛ ጠላት ድህነት መሆኑን ግልፅ ያደረጉ ብቻ ሳይሆኑ፣ ይህን የሃገርና የህዝብ ጠላት መሆኑን በማስረዳት በግንባር ቀደምትነት የተፋለሙና ያፋለሙ የሀገር ባለውለታ ናቸው። በዚህም ሀገራችንንና ህዝባችንን ወደ አዲስና ቀጣይነት ወዳለው ተከታታይ የዕድገት ጎዳና አሸጋግረውታል፣ የተረጂነት ዕድሜውም እንዲያጥር አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በህይወት ዘመናቸው ሁሉ በፅኑ ያምኑበትና አያሌ ተከታዮችንም ሊያፈሩ የቻሉበት አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ቢኖር በልመና እና በእርዳታ የዚህች ሃገር ልማት ሊረጋገጥ የማይችል ነው።

“በገንዘብ ሆነ በዕውቀትም ራሳችንን እስካልቻልን ድረስ ከውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ልናመልጥ አንችልም። የልማታችንን ፍጥነት ወሳኞችም እኛ ባለቤቶቹ ሳንሆን ሌሎች ይሆናሉ” የሚል አቋም ይዘው  የተነሱ ከመሆናቸው ባሻገር ወደተግባር የሚቀየርበትን መሰረት ለመጣል ችለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትራችን በዕውቀት በኩል ራሳችንን እንድንችል ከማድረግ አንፃር ምን ሚና ተጫውተዋል? የሚለውን ዕውነታ በምናይበት ጊዜ ትምህርት እንዲስፋፋና ጥራቱም የተጠበቀ እንዲሆን የወሰዷቸው እርምጃዎች ቀዳሚውን ስፍራ ይዘው እናገኛቸዋለን።

በትምህርቱ በኩል ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርፀው ተግባራዊ እንዲሆን አስችለዋል። በተጨማሪም ለመስኩ ያልተቋረጠ ክትትልና ድጋፍ በመስጠት ለዕድገቱ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል።

ከዚህ ጎን ለጎንም 'አቶ መለስ የቀየሷቸው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመስኩ ላይ ምን መሰረት ጥለዋል?' የሚለውን ጥያቄ በምናይበት ወቅት ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ ከምንም በላይ ሁሉም ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የትምህርቱ በእኩልነትና ፍትሃዊነት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ አስችለዋል።

በተመሳሳይ መልኩም ጥራቱን የጠበቀና ዓለም አቀፋዊ መስፈርትን ያሟላ ትምህርትና ስልጠና ተግባራዊ እንዲሆን መንገዱን የቀየሱም ናቸው። ሃገሪቱ ለምታካሂዳቸው የልማት ስራዎች አስፈላጊ የሆኑ የትምህርትና ስልጠና ዘርፎች እንዲጀመሩ፣ የትምህርት ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ፣ የመምህራን አቅም እንዲያድግ፣ ...ወዘተ መነሻም ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትራችን ትምህርት የእድገት መሠረት መሆኑን በፅኑ በማመን በወሰዷቸው እርምጃዎች ባለፉት አመታት ውስጥ ልማታዊ አስተሳሰቡ የዳበረ፣ በቂ እውቀትና ክህሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ሃይል በብዛትና በጥራት ለመገንባት ተችሏል።

ይህም በመጀመሪያ ደረጃ ህዝባችን ከኋላ ቀርነት እንዲላቀቅ አቅም ፈጥሮለታል። ሌላው ቀርቶ በገጠሩ አካባቢ ያለውን እውነታ ብንመለከት እንኳን፤ አርሶ አደሩ ከባህላዊ አሰራር ተላቆ ዘመናዊ የአመራረትና የአኗኗር ዘይቤን ሊከተል የሚያስችለውን እድል ፈጥሮለታል።

በዋነኛነት ደግሞ በማንኛውም የልማት መስክ ላይ በብዛት፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ከሃገር ውስጥ ገበያ ገዝቶ ለማስማራት ትልቅ አቅም ተፈጥሯል። በመሆኑም ዛሬ ሃገራችን በዕውቀት አግዙኝ እያለች የውጭውን ዓለም ደጅ የምትጠናበትና ረብጣ ዶላሮችን የምትገፈግፍበት አስገዳጅ ሁኔታ በሂደት እየቀነሰ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪም ለከፍተኛ ትምህርት ዜጎችን ወደ ውጭ ሃገር ልኮ ለማስተማር ካለው ውጣ ውረድና ከፍተኛ ወጪ ለመዳን የተቻለበት አቅም ላይ ለመድረስ ተችሏል።

ታዲያ ይህ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ግንባር ቀደምትነት የተጀመረው በዕውቀት ራስን የመቻል ስራ በተለይም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል።

ዘርፉን ለማልማት የተቀመጡት አቅጣጫዎች በሁለት ክፍሎች ሊታዩ የሚችሉ ናቸው። በአንድ መልኩ የአገልግሎቱን መጠን በማስፋፋት የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ማስፋት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት ስርዓቱ ከላይ እስከ ታች ድረስ ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው። ከዚህም አንፃር ባለፉት ሁለት የአፈፃፀም ዓመታት ውስጥ በትምህርት ዘርፍ ልማት በኩል የተከናወኑ ተግባራት ምን ይመስላሉ? ውጤታቸውስ? … ቀጥሎ የማነሳቸው ጉዳዩች ይሆናሉ።

የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዝግጅት መሰረት ያደረገው ሃገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ ስኬታማ ለማድረግ ለኢንዱስትሪው በተለይም በማደግ ላይ ያለውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የአጠቃላይ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርትን በተመጋጋቢነት በማስፋፋት በዕቅድ ዘመኑ ጥራቱና ፍትሃዊነቱ የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና ለማረጋገጥ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ይገኛል።

ባለፉት ሁለት አመታት የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥ በየእርከኑ የሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶችና የጉድኝት ማዕከላት በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት ደረጃውን ባሟሉ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች እንዲመሩ በማድረግ የትምህርቱን ጥራት የሚያረጋግጥ የአመራር ስርዓት ለመዘርጋት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

የየእርከኑን ትምህርት የሚያጠናቅቁ ሁሉም ተማሪዎች ከየእርከኑ የሚጠበቀውን የስነ ምግባር ባህሪያት የሚጨብጡበትን አግባብ ለመፍጠር የሚያስችል ተግባርም ለመፈፀም ተችሏል።

በሌላም በኩል በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ቢያንስ ሃምሳ ከመቶ አማካይ ውጤት የሚገኙ ተማሪዎችን ወደ ዘጠና ከመቶ ለማሳደግ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ የመምህራንን የብቃት ደረጃ ለማሳደግም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ተችሏል። በተጨማሪም የሁሉም እርከን ስርዓተ ትምህርቶች አስፈላጊውን ጥራትና አግባብነት ያረጋገጡ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል።

የትምህርት ፍትሃዊነትንና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እንዲሁ ባለፉት ሁለት ዓመታት በርካታ ስራዎች ተፈፅመዋል። በዚህ በኩል በዕቅድ ተይዘው ወደተግባር ከተሸጋገሩ ጉዳዮች መካከል በአብዛኛው ከዕቅድ በላይ ውጤት ለማስመዝገብ የተቻለ ነበር።

ለአብነት ያህል በቅድመ መደበኛ ትምህርት በ2002 ከነበረበት የ4 ነጥብ ሁለት በ2004 ወደ 12 ነጥብ አንድ በመቶ ለማድረስ በእቅድ ተይዞ

ወደተግባር ቢገባም በሃገር አቀፍ ደረጃ የተገኘው ውጤት ግን ከዕቅድ በላይ 16 ነጥብ ስምንት ሊደርስ ችሏል።

የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎን በተመለከተም በ2002 ከነበረበት 87 ነጥብ ዘጠኝ በ2004 ዓ.ም ወደ 91 ነጥብ አምስት ለማድረስ ታቅዶ ነበር ወደ ተግባር የተገባው። ይሁን እንጂ የተገኘው ውጤት ከእቅዱ በላይ የ5 ነጥብ ዘጠኝ ከመቶ ተጨማሪ እድገት ማለትም 97 ነጥብ አራት ለማስመዝገብ ተችሏል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያ ሳይክል ጥቅል ተሳትፎን በማሳደግ በኩልም በሁለቱም ዓመታት እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን፤ በዚህ በኩልም የተሻለ አፈፃፀም ሊመዘገብ በቅቷል።

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መስክ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት ውስጥ ለመድርስ አራት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል። ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የብቃት ደረጃ በምዘና አረጋግጦ ወደስራ የተሰማራ የቴክኒክና ሙያ ባለሙያ ካለበት 23 ከመቶ ወደ 36 ከመቶ ማድረስ ነው። በተቀመጠው ስትራቴጂ መሰረት ሃብት መፍጠር ያስቻሉ ቴክኖሎጂዎችን አንድ ሺህ 200 ማድረስም ሁለተኛው ግብ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በቴክኒክና ሙያ ሰልጥኖ ከሚወጣው ባለሙያ 75 ከመቶ የሚሆነውን ከስራ ጋር በማስተሳሰር ወደ ስራ እንዲገባ ማስቻል ያስፈልጋል። ከዚህ መሳ ለመሳም በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ለመሳተፍ ፍላጎትና ያለውና ለደረጃው የሚጠይቀውን መስፈርት ለሚሟላት የሚችል ዜጋ ሁሉ ለመሳተፍ የሚያስችል አቅም መፍጠር የሚሉ ግቦችን አስቀምጦ ነበር። በመሆኑም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ እነዚህን ሊያሳኩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል።

ከፍተኛ ትምህርት በኩል እንዲሁ በርካታ ተግባራት ተፈፃሚ ሆነዋል። ከዚህ አኳያ ትኩረት ተሰጥቷቸው በመተግበር ላይ ከሚገኙ ስራዎች ብቁ የመምህራን ኃይልን መገንባትና ለውጤታማነት ማብቃት አንዱ ነው።

በዚህ በኩል ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም በትምህርት ልቀታቸውና በመምህርነት ሙያዊ ክህሎታቸው እንዲሁም በሙያዊ ስነ-ምግባራቸው ምስጉን የሆኑና በማስተማርና በምርምር አንቱ የተባሉ፣ ከሃገር አልፈው በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ እስከ 23 ሺህ የሚደርሱ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ኃይልን ለመገንባት እቅድ ተይዟል።

ከእነዚህም መካከል እስከ 75 ከመቶ የሚደርሱት በሁለተኛ ዲግሪ የተቀሩት ደግሞ ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸውና በድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን የሚገኙ የተመራማሪ መምህራን እምብርት የሚሆኑ ናቸው። ከዚህ ግብ አፈጻፀም አኳያ በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት የተሰራው ስራ እጅግ የሚያኮራ ነው ለማለት ይቻላል። በአሁኑ ወቅት በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመምህራን ቁጥርን 18 ሺህ ለማድረስ ተችሏል።

በከፍተኛ ትምህርት በኩል በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ የተፈፀመው ሌላው አንኳር ጉዳይ፣ ልማቱ ከሚጠይቀው የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር ተገቢነት ያላቸውን የትምህርት መርሃ ግብሮችን ለይቶ ከማስቀጠልና አዳዲስ መርሃ ግብሮችን ከማስጀመር እንዲሁም የስርዓተ-ትምህርታቸውን ትክክለኛነት እያረጋገጡ ከመሄድ አንፃር የተከናወነው ተግባር ነው።

ከዚህ በመነሳት በከፍተኛ ትምህርት እየተሰጡ ያሉ የትምህርት መርሃ ግብሮች ከሃገሪቱ ፍላጎት ጋር ተጣጥመው እንዲሄዱ በተደረገው ጥረት ከአሁን በፊት ያልነበሩ እንደ የባቡር፣ የመንገድ ምህንድስና፣ የስኳር አመራረት ቴክኖሎጂና ምህንድስና፣ የተለያዩ የስፖርት አይነቶች አሰልጣኝነትና ዳኝነትና …ወዘተ የመሳሰሉት ፕሮግራሞችን እንደ አዲስ ለመጀመር ተችሏል።

የእነዚህ አዳዲስ የስልጠና መስኮችን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ያለፉት ሁለት ዓመታትን ስንመለከት፤ በመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ በኩል ለዘርፉ ወሳኝነት ያላቸውን የስልጠና መስኮች በመለየት የአምስት የመንገድ ምህንድስና ስልጠናዎችን በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ለመስጠት የሚያስችሉ ዝግጅቶችን በመፈፀም ከአምስት መቶ በላይ ተማሪዎች ሦስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ገብተው በመማር ላይ ይገኛሉ።

ከባቡር መሠረተ- ልማት ግንባታ አኳያ እንዲሁ ለዘርፉ የሚያስፈልጉ የስልጠና ሙያዎችን በመለየት ስድስት የባቡር ምህንድስና ስርዓተ ትምህርቶችን በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ለማዘጋጀት ተችሏል።

ሌላው ዕመርታ የስኳር አመራረት ቴክኖሎጂና ምህንድስና ነው። ለዚህ ዘርፍ የሚያስፈልጉ የስልጠና ሙያዎች ተለይተው በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ፣ በስኳር ምህንድስናና በስኳር ተክሎች አመራረት በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ለማሰልጠን የሚያስችሉ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃና ሌሎች ዝግጅቶችን የሰመራ፣ የአርባ ምንጭ፣ የጂማና የወለጋ ዩኒቨርሲቲዎች በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በቀጣይነት በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ለመሰልጠን ፍላጎት ያላቸው ሃምሳ የሚደርሱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአራተኛ ዓመት የኬሚካል ምህንድስና ተማሪዎች ወደ ሦስቱም ነባር የስኳር ፋብሪካዎች በማሰማራት የመስክ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ተደርጓል።

በስፖርት በኩል አስራ ሦስት ስርዓተ- ትምህርቶች በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ተቀርፀው እየተጠናቀቀ ካለው ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ መደረግ ጀምረዋል። በተጨማሪም በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የሚሰጡ አስራ ሦስት ስርዓተ - ትምህርቶች ቀረፃ ተጠናቆ ወደተግባር በመሸጋገር ላይ ይገኛሉ።

በከፍተኛ ትምህርት መስክ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ከሃገሪቱን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ስኬታማ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታ ያላቸውን አዳዲስ የስልጠና መርሃ ግብሮችን ቀርፆ ተግባራዊ ተደርጓል።

ከዚህ ጎን ለጎንም ነባሮቹን የትምህርት ዘርፎች ጥራት ለማረጋገጥ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ከዚህም ባሻገር በአንዳንድ የስልጠና መስኮች የሚሰለጥነውን የሰው ኃይል ቁጥር ከሃገሪቱ ፍላጎት ጋር ለማጣጣም እርምጃዎችን ለመውሰድ የተቻለበት ሁኔታ ነው ያለው።

ከዚህ አኳያ ተጠቃሽ መሆን ከሚችሉት የስልጠና ሙያ መስኮች አንዱና ዋነኛው የህክምናው ዘርፍ ነው። እንደሚታወቀው የህክምና ሙያ ስልጠና በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ሲሰጥ የነበረና እየተሰጠ ያለ ቢሆንም ሃገሪቱ ከሚያስፈልጋት የሰው ሃይል አንፃር ግን አጥጋቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም በዘርፉ የሚሰማራውን የሰው ሃይል ለማሳደግ በርከት ያሉ ተማሪዎችን ማብቃት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል።

ከዚህም በመነሳት የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጋራ በጀመሩት መርሃ ግብር፣ አዲስ የሃኪሞች ስልጠና ስርዓት ተዘርግቶ ለመጀመሪያ ጊዜ 950 ተማሪዎች በአስር ዩኒቨርሲቲዎችና በሦስት ሆስፒታሎች ትምህርታቸውን ከ2004 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በመከታተል ላይ ናቸው።

በጥቅሉ ከከፍተኛ ትምህርት ጋር በተያያዘ በሁለቱ ዓመታት የተከናወነው የስርዓተ ትምህርቶችን ተግባራዊነት ማረጋገጥ ነው። ለዚህም የተግባር ልምምድ ቁልፍ መሳሪያ ሆኖ ይገኛል። ምክንያቱም ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በክፍል ውስጥ የወሰዱትን ትምህርት በተግባር ማየታቸው በአንድ በኩል ስርዓተ ትምህርቱ ትክክለኛና ተግባር ላይ ሊውል የሚችል መሆኑን ለመፈተሽ የሚያስችል ስለሆነ ነው። በሌላም ጎኑ ደግሞ ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ የቀሰሙትን እውቀት በተግባር እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል።

በተለይ ተግባር ተኮር የሆነውን አዲሱን የምህንድስና ትምህርት ፕሮግራሞች ስርዓተ- ትምህርት ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የአንድ ሙሉ መንፈቅ ዓመት የስራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም በ2003 ዓ.ም በሰባት የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች (ማለትም በኢትዮጵያ አርክቴክቸር፣ ህንፃ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ባህር ዳርቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳትና ፋሽን ዲዛይን ኢንስቲትዩት፣ በመቀሌ፣ ጂማና ኮምቦልቻ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች) ተግባራዊ ተደርጓል። ባለፈው አመትም በድሬዳዋ፣ በአርባ ምንጭና በሐዋሳ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችም ተፈፃሚ ሆኗል።

በድምሩ በባለራዕዩ መሪያችን የተጀመረውና በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ውስጥ በትኩረት መፈፀም የቀጠለው የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ልማት ታላቅ እመርታን በማስመዝገብ እነሆ የዕቅዱ ሦስተኛ ዘመን ላይ ሊደርስ ችሏል።

እርግጥ ከእነዚህ እመርታዎች የትምህርትና ስልጠናው ዘርፍ እጅግ የሚያኮራ ወጤትን እያስመዘገበ ለመሆኑ መስካሪ አያሻውም። ታዲያ በያዝነው የበጀት ዓመትም እንዳለፉት ጊዜያቶች ሁሉ ጊዜያት ግለቱን ጠብቆ እንደሚጓዝ እሙን ነው። አዎ! ያለፉት ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፤ አዳዲስ ዕቅዶችም ወደ ተግባር መመንዘራቸው አይቀሬ ነው። እስቲ ለማንኛውም የዚያ ሰው ይበለን።…